



NES Commentary No.48

NB: This is a message on the current grand renaissance dam written by the acting director of the Ethiopian Women Association in Southern Africa. The key message is that the electricity provision from the completion of the Grand Renaissance Dam(GERD) will liberate all our women who struggle very hard with wood and fuel to make all the families to survive. The young and dynamic sister Dagmawit Aynalem has written a message to encourage all the people to unite and all our women in Ethiopia from children to the aged to join together and support the earliest possible completion of GERD. I encourage you to read her message and send her your feedback to her: e-mail: dagmawita@yahoo.com

Also all Ethiopians must support to make sure the wellbeing of all our women and all the people is secure. The time must come where we never witness our women exposed to all kinds of risk as we keep witnessing in the Middle East. Let us all unite and support all our Ethiopian women by valuing them as our sisters and mothers. ( https://sarchi.org/?p=772) & www.sarchi.org

**ከ ሳዉዝ አፍሪካ የኢትዮጵያዉያን ሴቶች ማህበር (EWASA)**

**አባይ ከሰው ስምነት እና ከዘፈን ማድመቂያነት ወቶ የሃገር መመኪያ ወደብ ከድህነት የመዉጪያ ተስፋ እና በብዙ የሃገራችን ገጠር እና ከተማ ለሚኖሩ ወገኖቻችን ጨለማን ገፎ ብርሃን የሚያጎናጽፍል ትልቅ ተስፋ ሊሆንልን እንደሆነ ያበሰረኝን ዜና የሰማዉበትን ቀን መቼም አልረሳዉም።**

**እኔም ድርሻዬ ምንድነው እል ነበር?**

በብዙ ከወጣንበት ማህበረሰብ አኳያ ሴት ልጅ ለፖለቲካና ሃገር ነክ ለሆኑ ጉዳዮች የምታሳየዉ ተሳትፎ በጣም ኢምንት ነው። እንዲሁም ባሁኑ ጊዜ ለየት ባለ ሁኔታ በዛ ብለው ስልጣን ይዘው እየመሩን ያሉትን ሴቶቻችንን ሰብሰብ ብለን ጥሩ አጋዥ እና ተመሪ እንሁናቸው ልል እወዳለው።

በስደት ላይ ያለነው ሴቶች ደግሞ በጣም ብዙ መከራንንና ችግርን ስላሳለፍን የሃገርን ፍቅር ለመግለፅ ከኛም በላይ ብል ማጋነን አይሆንብኝም።

***ሃገራችን ለኛ ዞሮ መግቢያችን አለኝታችን፣ መመኪያችን፣ የኩራታችን ምንጭ ናት።*** *ታዲያ ይህንን ለሚያክል ቦታ ለምንሰጠው ህልውናችን የእያንዳችንን ምላሽና ለአገራችን አለዉልሽ እማማ የምንለው እንዴት ነው?*

**አንድነትን እንሰበክ።**

- የጋራ ጠላትን እንዋጋ፣  የእቴጌም ልጆች አደለንም እንዴ? የጣይቱ ቡጡል
- አገርን የሚጠቅሙ ድርጊቶች ላይ እንሳተፍ፣ ባለን እውቀት አቅም ምንም ሳንሰለች፣
- አዎንታዊ ተፅአኖ አምጭዎች ለመሆን እንጣር።

**የሚምያርብን አንድነት ነው በሱም ተገምደናል።**

- ወደ ዋናው ወደመጣንበት ጉዳይ ስንገባ  የህዳሴ ግድብ ነው እዚህ ያገናኘን።

በጣም ብዙ ፅሁፎችን እና ንግግሮችን ከሰሞኑ ለማንበብና ለማዳመጥ የመቻል እድልን አግኝተናል። ይህም የእውቅት አድማሳችንን አስፎቶታል ብል ዉሸት አይሆንም፣ አባይን ከአንድ የአገር ሃብት፣ መግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት እንዲሁም ከህብረተሰብ አና ታሪክ ትምህርት ባሻገር ሉአላዊነታችን እንደሆነ እንዳገናዝብ እናም በምችለው አቅም ድምፄን ለማሰማት እንድጥር አድርጎኛል። ለዚህም የፕሮፈሴር ማሞ ሙጨን የሚያስቀና የሃገር ፍቅርን ሳልናገር ማለፍ አልሻም።

አገርን በቀጥታ እንዲሁም በተዘዋዋሪ ሊጎዱ የሚችሉ ክንዉኖች ላይ አብዛኛው ተጠቂ ሴቶች ናቸው። ሴት ልጅ የቤት ምሶሶ ናት፣ የሴት ልጅ ተፅዕኖ ብዙ ነው። ከእንጨት ለቀማ አንስተን፣ አይናቸው ጭንብስ ብሎ ምግብ፣ አብስለው፣ እንጀራውን በእንጨት ጋግረው፣ የዚህ እና የመሳሰሉት በሙብራት እጦት ለሚመጡት እንቅፋቶች አብዛኛው ተጠቂ ሴት ናት፣ ታዳጊ እህቶቻችን ናቸው። እናት ናት ።



©Twitter

**እናቶቻችንን እንደዚህ በጭስ ከመጨናበስ የሚታደጋቸው ብቸኛው ተስፋቸው የህዳሴ ግድብ ነው።**



©Twitter

- የህዳሴ ግድብ ቢገደብ 65ሚልዮን በላይ የሆነው ህዝባችን የመብራት ተጠቃሚ ይሆናል በነዚህ ቤቶች ውስጥ ሁሉ ስንትና ስንት ሴቶች አሉን?
- 2/3 የሚሆኑ ተማሪዎች በጨለማ ውስጥ ነው ያሉት፣ እህቶቻችን እና እናቶቻችን ለማብሰያ ዉሃ እና እንጨት ለቀማ ረጅም ሰአት እየተጓዙ ነው ያሉት፣ ይህም ለብዙ በጣም እየተስፋፋ ለመጣው ሶታዊ ጥቃት እናም አካላዉ ጉዳት አጋልጧቸዋል። በጭሱ የስንቱ እህቶቻችን እና እናቶቻችን አይንስ ተጎድቶአል? ሆድ ይፍጀው። የህዳሴው ግድብ ይህንን የማስወገድ አቅም አለው።

**ሴትን ልጅ ማስተማር፣ ከድህነት ማዉጣት በተዘዋዋሪ አገርን ማሳደግ ነው። አገር ከቤት ነው የሚጀምረዉና።**

ግድቡ የኔ ነው ስንል በምክንያት ነው። ከሃገራችን በሚፈሰው የውሃ ሃብት ምንም ሳንጠቀምበት እንከዛሬ ለሌሎች ሃገራት ስናበረክት ኖረናል። የተፈጥሮ ሃብታችንን ለራሳችን መጠቀም መቻል አለብን። ይህንንም ከግብ ለማድረስ ከ 2012 ጀምሮ መገንባት የተጀመረው (የህዳሴው ግድብ) ሁላችንም እንደምናቀው ፍፃሜዉን እስካሁን አላገኘም። ለዚህም ከምንጊዜዉም በላይ አገራችን ልዩነታችንን ወደ ጎን አርገን የአባይን ልጅ ዉሃ ጠማዉ ሲባል አድገን ሲባል እንዳንሞት የዜግነት ግደታችንን እንድናሟላ ጠይቃናለች። ለአምዬ ይህም ሲያንሳት ነው።

አገራችንን ወክለው ክብራችንን ለማስከበር ከተባበሩት መንግስታት፣ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከአረብ ሊግ፣ ከዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ፣ ከአለም ባንክ በተለያዩ መድረካት ላይ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ አቋማችንን ጥበብ በተሟላበት  መንገድ እየተሟገቱልን ያሉት ከኛ የሚጠብቁት አንድ ነገር ቢኖር አንድነትን ነው።

__እነሱንም በዚህ አጋጣሚ ላመሰግን ወዳለው።ውለታችሁ አለብን።__



©Twitter

አባይ ቢገደብ ግብፅን ይጎዳታል? ግብፅ እያለች እንዳለችው ከጥቂት አመታት በሁላ ድርቀት ሊያጋጥማት ይችላል? ሌሎቹ የናይል ተፋሰስ አገራትን?

ባጭሩ ለመመለስ ያህል **አይጎዳቸዉም**፣ ግብፅ ከናይል የምታገኘዉን ዉሃ በተለያዩ ጊዘያት በምን፣ የት፣ እንዴት፣ እንደምታዉለው ተጠይቃ ለመመለስ ፈቃደኛ አደለችም በደፈናዉ ዉሃው የኔ ነው ከማለት በቀር። ይህም ፍላጎቱዋን ግልፅ አርጎታል። ግድቡን መሙላት የኛ ሙሉ መብት እንዳለ ሆኖ ለኛ የኤሌክትሪክ አቅም ብቻ አይደለም የሚያስገኝልን። ባልተጠበቀ፣ ቁጥጥር ያልተደረገበት ጎርፍ የሚመጣዉን አፈር ወደ ግብፅና ሱዳንም የሚሄደዉን ወደ 86% የሚሆን ደለል እና ዝቃጭ ያጣራል የውሃውን መዉረድ በጎርፋማ ወቅት መቆጣጠር ያስችላል ።ከሱም ባሻገር ወደ ተፋሳሽ ሃገራት የሚወርደዉን አላስፈላጊ የሆነ ጎርፍን የመታደግ ብቃት አለው። ባልተጠበቅ የአየር ንብረት ሊመጣ ከሚችል ድርቅ ሊታደገን ይችላል። ከተከማቸው ንፁህ ውሃ ላይ በከፉ ጊዜ ለጎረቤቶች አገራት ለማካፈል የሚችል አቅምም አለው። ግድቡ መገደቡ የውሃዉን አጠቃቀም በመቆጣጠር ይህንንም ፍሰቱን በድርቃማም በጎርፋማ ጊዜያት ለመቆጣጠር ያግዛል። የዉሃው ማጣሪያው መካኒንክም ከትነት እና የአየር ንብረት ለዉጥ ሊመጣ የሚችለዉን ከባድ አደጋና እጦት የመታደግ አቅም አለው። የግድቡ መገደብ እና በስራ ላይ መዋል ይህንን እና ሌሎች ጥቅሞች ለናይል ተፋሰስ አገራት አለው።

ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው ሉአላዊነታችንን እናስከብር፣ ኢኮኖሚያችንን እናሳድግ፣ ከድህነት እንዉጣ ስንል ለሎቹን አየጎዳን አደለም። የኛ ግን የኛ መሆን አለበት። ታሪክም በግልፅ እንዳስቀመጠው እጅ ሰተንም አናውቅም። ሰሞኑን በማህበራዊ ገፆች ላይ ***"ግድቡ የኔ ነው"*** የሚል መሰላል በመጠቀም አንድ መሆናችንን አሳይተናል። እዚህም በሳውዝ አፍሪካ እና አካባቢዋ ያለነው እትዮጵዉያን እና ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን ዝም አንበል፣ ድምፃችንን እናሰማ፣ የፕረዝዳንት ሲርል ራማፕሆሳ የአፍሪካ ዩኒየን ቼር መሆኑ ለኛ ትልቅ አስተዋፃ አለዉ በጋራ ድምሳችንን ብናሰማ በአገሪትዋም ሚዲያዎች ላይ አሉታዊ ምላሽን ለማግኘትና የአፍሪካን ጉዳይ በአፍሪካዊ መፍታት የሚለዉን መንፍስን እናጎለብታለን።

ለሁሉም እንደርሰበታለን ለልዩነታችን፣ ገዢዉን መንግስት ደገፍን ማለት አይደለም።

- ከዛ ይልቅ እናቶቻችንን እህቶቻችንን ታዳጊዎችን ከጭስና ከወገብ ስብራት አተረፍን
- የተማረ ብዙ ሃይል ይኖረናል።
- እህትህንና ወንድማችንን ከጭለማ ታደግን ማለት ነው።

ከሱም ባሻገር አገራችን በኢኮኖሚና ፖለቲካ ቀዳሚነትዋን በምትቀዳጅበት ሰአት ስደትም እንደሚቀንስ ጥርጥር የለኝም። ግድቡን መሙላት እንጀምር፣ እንጨርሰው የምንለውም ለዚም ነው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

***ሁላችንም ለአገራችን አፈር ያብቃን።***

ዳግማዊት አይናለም

ሰኔ 2020



© Twitter